# የአዳማውም ክስተት የወያኔ አጠቃላይ ፖሊሲ አካል ነው፤ ምላሹን የምንሰጠውም ራሱ ወያኔን በማስወገድ ነው

የግንቦት 7 ድምጽ ቁጥር 67 ርዕሰ አንቀጽ

ከግንቦት 1997 ወዲህ ‹‹ምርጫ›› የሚለው ቃል ብቻውን ወያኔን ያሸብረዋል። እንኳንስ የምር የውሸት ተፎካካሪ እንኳን በሌለበት ሁኔታም ቢሆን በምርጫ ወቅት ወያኔ መደናበሩ አይቀርም። ይህንን ደግሞ በአለፈው ዓመት ‹‹የአካባቢና የማሟያ ምርጫ›› በተሰኘው ከሶስት ሚሊዮን በላይ ሰዎች በተመረጡበት አስቂኝ የምርጫ ተውኔት በግልፅ የታየ ሐቅ ነዉ። በዚያ ምርጫ ከተወዳዳሪዎቹ ዘጠና አምስት በመቶ ያህሉ ወያኔዎችና ምስለኔዎቻቸው ነበሩ። ያም ሆኖ ግን ወያኔ ‹‹ምረጡኝ›› እያለ ሰውን ማንገላታቱ፤ ከአስር ሺህ ተወዳዳሪዎች ውስጥ አንድ የወያኔ ተቃዋሚ ከተገኘ እሱኑ ማዋከብ ሥራዬ ብሎ ይዞት እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው።

በግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት የነፃ ተቋማት መኖር ከምርጫ በላይ አስፈላጊ ነገር ነው። ነፃ ተቋማት ካሉ አንድ ምርጫ ቢበላሽ በሌላ ምርጫ ይስተካከላል፤ ተቋማቱ ከሌሉ ግን ምርጫ የለም። ከምርጫ 97 የተማረነው ትልቁ ትምህርትም የነፃ የተቋማት ሚና ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ነው። ከምርጫ 97 ወዲህ ደግሞ የወያኔ ተቋማት ይበልጥ አፋኝና በሚያሳፍር መልኩ ከቀድሞው የባሰ ዘረኛ ሆነዋል። በዚህም ምክንያት የ2002 ዓ.ም አገራዊ ምርጫ እየተቃረበ ሲመጣ የወያኔ መደናበር የሚፈጥራቸው አሳዛኝ ክስተቶችን መታዘባችን አልቀረም። ነሐሴ 10 ቀን በአዳማ ከተማ በአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ መሪዎች፣ የክብር እንግዶቹና ደጋፊዎቹ ላይ የደረሰው እንግልት ከእነዚህ ክስተቶች ከመጀመሪያዎቹ አንዱ ነው፤ ወደፊት ከዚህም የባሱ አሳዛኝ ክስተቶ እንደሚኖሩ መጠበቅ ብልህነት ነው።

ጉዳዩ በአጭሩ የሚከተለው ነበር፡፡ ነሐሴ 10 ቀን 2001 ዓ.ም አንድነት ፓርቲ በአዳማ ከተማ የጠራው ስብሳባ ሲጀመር የወያኔ ምስለኔ የሆነው የኦህዴድ ካድሬዎች ‹‹ነፍጠኛ በምድራችን ላይ አይንቀሳቀስም፣ ለነፍጠኞች አሳልፎ የሸጠንን ነጋሶን ማየት አንፈልግም፣ ሴት ልጅ በመድረክ ላይ ወጥታ ንግግር ማድረጓ የኦሮሞን ባህልና ሕዝብ መናቅ ነው፣ ነፍጠኞች በአማርኛ ቋንቋ አንሰማችሁም! ስብሰባው በሸማግሌ ምርቃት መከፈት ነበረበት! …›› ሌላም ሊጻፉ የማይገባቸው አስነዋሪ ቃላትን በመናገር በተቀነባበረ ጩኸትና ፉጨት ስብሰባው እንዲቋረጥ አደረጉ። የስብሰባው አዘጋጆችና እንግዶች ከአዳራሹ የወጡት የስድብ ናዳ እየወረደባቸውና በመገፍተር ጭምር ነበር።

ይህ የአዳማው ክስተት፡-

1. ወያኔ ዘረኝነትን ለምስለኔዎቹም በማስተማር እኩይ ሥራው በተወሰነ መጠን ውጤት እያስመዘገበና ራሱን የመሰሉ ዘረኞች በየቦታው እያመረተ ስለሆነ የኢትዮጵያ አገራችን ሕልውና አደጋ ላይ መሆኑ፤
2. ጉልህ የሆነ ስጋት ባይኖርበትም እንኳን ወያኔ በለስላሳ ተቃዋሚዎቹ ላይ ሳይቀር ምን ያህል ነውረኛ ተግባር የመፈጸም አቅል እንዳለውና ከዚህም በላይ ከመፈጸም የማይመለስ እርኩስ መሆኑ፤

3. ሕብረተሰቡን በእለት ተእለት ተግባር ማገልገል ያለባቸው የፓሊስና የቀበሌ ጥበቃ አባላት ሳይቀሩ ምን ያህል ወገንተኛ መሆናቸውና ወያኔ ፊታቸውን ያጠቆረባቸው ሰዎች በማጅራት መቺዎች ቢመቱ እንኳን ደርሶ የሚያስጥላቸው የሌለ መሆኑን፤ እና
4. ባጠቃላይ በአገሪቷ ውስጥ ህግ የሚባል ነገር ፈጽሞ መጥፋቱን ያመለክታል።

የአዳማው ክስተት የተፈፀመው የ2002 የቅድመ-ምርጫ ዘመቻ ገና ተፋፍሞ ሳይጀመር መሆኑ ዘመቻው ሞቅ ካለ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ፍንጭ የሚሰጥ ነው። ከአዳማ በፊትም በመቀሌ አረና ትግራይ፤ በባህርዳር ደግሞ አንድነት በጠራቸው ስብሰባዎች ላይ ተመሳሳይ ፍንጮች ተስተውለው ነበር። ስለሆነም የአዳማው የተናጠል ክስተት አይደልም። የአዳማው ክስተት የወያኔ ኢትዮጵያን የመግዣ ትልቁ ፓሊሲ አካል እንጂ በተለይ ከአዳማ ከተማ ወይም ከኦሮሚያ ክልል ወይም ከኦሮሞ ማኅበረሰብ ጋር የሚያያዝ አይደለም። ነገ በጋምቤላ፣ በአሶሳ፣ በጅጅጋ፣ በሐረር፣ በድሬዳዋ፣ በአሳይታ፣ በደሴ፣ በጎንደር .... በማናቸውም የኢትዮጵያ የክልል ከተሞች የተቃማዊ ፓርቲዎች ስብሰባ ከጠሩ ተመሳሳይ ወይም ከዚህ የባሱ ነገሮች መፈፀማቸው አይቀርም። ትንሽ ቆይቶ ደግሞ አዲስ አበባ ውስጥም ይፈፀማል  ይህ የምናውቀው የወያኔ ባህሪይ ነው።

ግንቦት 7 ነፃ ተቋማት ሳይኖሩ ምርጫ ውስጥ መግባት ለእንደዚህ ዓይነት ስብእናን ለሚያዋርዱ፤ የሕዝብን ሞራልና ስነልቦና ለሚጎዱና በአገራችን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት የምናደርገውን ጥረት ለሚያወሳስቡ ጥቃቶች እንደሚያጋልጥ ከመግለጽም አልፎ መፍትሂውንም አመላክቷል።

ይህንን በአገርና በህዝብ ላይ የሚፈፀም ወንጀል ለመከላከል መፍትሄው የወያኔን ጨዋታ አለመጫወት ነው ብሏል። ዳኛ እንደሌለ፤ ተፎካካሪው ጠበኛና ነውረኛ እንደሆነ እየታወቀ ጨዋታ ውስጥ ከተገባ በኋላ ‹‹ተገፋሁ፣ ተረገጥኩ›› ተብሎ ለማን አቤት ይባላል? ለጊዜው ጨዋታውን አለመጫወት መብት ስለሆነ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ በትኩረት እንዲያጤኑት እንመክራለን። ወያኔ ይህንን መብት ሊገፍ እንደሚችልና በግድ ‹‹ተወዳድራችሁ ተሸነፉ›› ሊል እንደሚችል በጊዜ ማወቅ ይበጃል እንላለን። ዋነኛው መልእክታችን ግን በምርጫው ተሳትፈን ለውጥ እናመጣለን  ብለው ለሚያስቡት ፓርቲዎች ሳይሆን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነው።

በአዳማ የተፈፀመው ድርጊት እጅግ አሳስቦናል። ስጋታችን ከኢትዮጵያ ህልውና ጋር እንጂ ከምርጫ 2002 ጋር የተያያዘ አይደለም። የወያኔ ‹‹ከፋፍለህ ግዛው›› ፓሊሲ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የራሳቸው ያደረጉ ግለሰቦችንና ቡድኖችን በየቦታው ተራጅተዋል። በዚህ ከቀጠለ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሁሉም ‹‹የኔ ከተማ የኔ ብቻ!!!›› እንዲል ይደረጋል። ይህ ደግሞ የወያኔ ህልም የሆነው የኢትዮጵያን መጥፋት እውን ያደርጋል፤ በምትኳም የሚመጡ ሌሎች አገሮች አይኖሩም። ይልቁንስ እርስ በርሳችን ስንጣላ ወያኔ ያለተቀናቃኝ አገራችንንም እኛንንም ይበላል። ይህንን አደጋ ነው ዛሬ ማስቆም ያለብን። የወያኔ መጫወቻዎች መሆናችን ሊያሳፍረንና ሊያንገበግበን ይገባል እንላለን። በምንም ሁኔታ ይፈፀም ምርጫ 2002 ለዚህ መፍትሂ አይሰጠንም። ዘላቂ መፍትሄው ወያኔን አስወግደን በነጻ ምርጫ በሚመጣ መንግሥት አማካይነት ችግሮቻችንን በሰላማዊ መንገድ የምንፈታበት ሥርዓት ማቆምና ለዚህ የሚረዱ ተቋማትን መፍጠር ነው። ይህ ነው የግንቦት 7 ተልእኮ።

ወያኔ በድንበር፣ በሃይማኖት፣ በዘር፣ በፓለቲካ እንዲያው ባገኘው ሰበብ ሁሉ ሊያፋጅን ይሻል። ይህ መላዋን ኢትዮጵያ የመቆጣጠሪያ ፓሊሲው አካል ነው። የአዳማውም ክስተት የወያኔ አጠቃላይ ፓሊሲ አካል ነው፤ ምላሹን የምንሰጠውም ራሱን ወያኔን በማስወገድ ነው።